# ፖሊሲ

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

**ተዛማጅ ፅሁፎች፡-** CND, JNA-RA, IPD-RA
**ኃላፊ ጽ/ቤት፡-** ዋና የሥራ አስፈፃሚ/Chief Operating Officer

## የተማሪዎች ስርአተ-ትምህርታዊ ወጪዎች

**A. ዓላማ**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ለሁሉም ተማሪዎች፣ የኢኮኖሚያዊ ሁኔታቸውን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ፣ የሁሉንም የትምህርት አይነቶች ሙሉ በሙሉ ለመክፍት፣ ለትምህርት አይነቶቹ የሚያስፈልጉ ትምህራታዊ ግባቶችን እና የትምህርት ፕሮግራም መቅረቡን ለማረጋገጥ

ከተማሪዎች የትምህርት ስርዓት ጋር የሚገናኙ ወጪዎችን በሚመለከት መከተል የሚገቡ ግቦችን ለማስቀመጥ

**ለ. አቋም**

1. የት/ቤት ስርዓቱ ማቅረብ የሚገባው፡-

   ሀ) የትምህርቱን ውጤቶች ለማሟላት የሚያስፈልግ የይዘት ግብዓትን እንዲያገኙ ማድረግ

   ለ) የደህንነት መጠበቂያ እቋዎች ለሚያስፈልጋቸው የትምህርት አይነቶች በሙሉ እቃዎቹን ማቅረብ

   ሐ) ያለክፍያ ለእያንዳንዱ ተማሪ ሦስት ግልባጮች

2. አጋዥ ግብዓቶችን ተማሪዎች እንዲገዙ ሊጠየቅ ይችል ይሆናል። ለአጋዥ ግብዓቶችን ምክንያታዊ በሆነ መጠን ማግኘት ለማንኛውም ተማሪ ሊከለከል አይችልም።

3. ተማሪዎች ለትምህርት ስርዓት ወይም አጋዥ ግብዓቶች መክፈል ስላልቻሉ ከትምህርታቸው ተዛማጅ በሆነ መንገድ አይቀጡም።

4. እንደ የቤተሰብ እና የተገበያይ/የተጠቃሚ ሳይንስ፣ የሙያ እና ቴክኖሎጂ ትምህርት፣ አርት፣

ቲያትር እና ሙዚቃ ያሉ የትምህርት አይነቶች ላይ ተማሪ በግል የሚሰራው/የምትሰራው ፕሮጀክት እንደ የግል ንብረታቸው ነው የሚሆነው። በእነዚህ ሁኔታዎች፣ የትምህርት ስርዓት ወጪዎች ክፍያ ሊጠየቅ ይችላል። ወጪው ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት በተማሪ እና አስተማሪ መካከል ተመጥኖ መቀመጥ አለበት፣ ወይም ቀድሞ በተተመነ የትምህርት ክፍያ ውስጥ መካተት አለበት።

5. ተማሪ አቅርቦቶችን ወይም መሳሪያዎችን ባልተገባ ንዝህላልነት/ዝንጉነት ቢያ(ብታ)በላሽ ወይም ቢ(ብት)ሰብር፣ በደንቡ መሰረት ለት/ቤት ስርዓቱ ወጪውን መልሶ የመክፈል ሀላፊነት የተማሪ ይሆናል።

6. የላብራቶሪ ክፍያዎች ሊጠየቁ ይችላል፣ ነገር ግን፣ ማንኛውም ተማሪ ክፍያ መክፈል ባለመቻል የተነሳ የላብራቶሪ ክፍያ በሚያስፈልገው ትምህርት ላይ ከመሳተፍ አይታገድም።

7. እያንዳንዱ ት/ቤት ከደንቡ ጋር በሚሄድ መልኩ በተገቢው የማህበረሰብ የበላይ ሀላፊ የተፈቀደ በትምህርት አይነት፣ በትምህርት ርዕስ ወይም በተጨማሪ ከትምህርት ተዛማጅ ነገሮች ከፋፍሎ የትምህርት ስርዓት ወጪዎችን ማዘጋጀት እና ማሳተም/ማሳወቅ አለበት። ወጪዎች በአመታዊ ሆነው መቀመጥ አለባቸው።

8. ት/ቤቶች ከትምህርታዊ ፕሮግራም ጋር የሚዛመዱ የመስክ ጉዞዎች ለተማሪዎቻቸው እንዲያቀርቡ ይበረታታሉ። ክፍያውን መክፈል ባለመቻል ምክንያት ከትምህርታዊ ፕሮግራም ጋር ተዛማጅ የሆኑ የመስክ ጉዞዎች ላይ ተማሪዎች በተናጠል እንዳይሳተፉ አይደረጉም።

9. ተማሪዎች በትምህርት አመታቸው ውስጥ ከትምህርት ስርዓታቸው ጋር የማይገናኙ እና የተማሪ የግል ሀላፊነት የሆኑ ሊያወጧቸው የሚችሏቸው በግል ምርጫ የሚወሰኑ ወጪዎች ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህ ወጪዎችም ሊያካትቱት የሚችሉት በግል ፍላጎት የሚደረጉ ግዢዎችን፣ እንደ የአትሌቲክስ ጫማ፣ የት/ቤት ጋዜጣ፣ አመታዊ መፅሀፍት (yearbooks) እና የክፍል ቀለበቶች አይነት ናቸው።

### ሐ. *ግምገማ እና ሪፖርት ማድረግ*

ይህ ፖሊሲ የሚገመገመው በትምህርት ቦርድ የፖሊሲ ግምገማ ሂደት መሰረት ነው።

*የዚህ ፖሊሲ ታሪክ፡-* የውሳኔ ቁ. 792-71፣ ዲሴምበር 14፣ 1971፣ በውሳኔ /Resolution 333-86 አንፃር ማስተካከያ የተደረገበት፣ ጁን 12፣ 1986፣ እና 456-86፣ ኦገስት 12፣ 1986፣ ተቀባይነት ያገኘው በውሳኔ ቁጥር/ Resolution No. 518-86፣ ሴፕቴምበር 22፣ 1986፤ ማሻሻያ የተደረገበት በውሳኔ ቁጥር/ Resolution No. 364-03፣ ጁላይ 8፣ 2003።

